በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ



በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከኦገስት 1-10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ እና

# ከኦገስት 11-20፣ 21-31/2026 የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ

# ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2026

አዲስ አበባ


## 1. እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል ባህር ዳር 36.1፣ ደብረ ማርቆስ 32፣ 36.6፣ 34.4፣ ጎንደር 41.3፣ ጅማ 32፣ 50.7፣ ነቀምት 60.3፣ 61.4፣ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 32.6፣ አደዋ 39፣ አማን 48.7፣ አምደወርቅ 49.9፣ አርጆ 36.2፣ አክሱም 43፣ አይከል 32.7፣ ባቲ 40፣ ቡሬ 32.4፣ ቻግኒ 54.3፣ ጨፋ 34.4፣ 38.7፣ ጨዋቃ 40.2፣ ጭራ 31.8፣ ደባርቅ 37.4፣ ደብረታቦር 30.4፣ 33.9፣ 34.5፣ ደብረ ወርቅ 33.9፣ ደምቢዶሎ 30.3፣ 40.3፣ ኢጃጂ 33.2፣ ፍቼ 37.2፣ ፉኙዶ 34.2፣ ጋምቤላ 35.6፣ 30፣ ጊዳአያና 54.1፣ ጊምቢ 36.6፣ 38.7፣ ጉንዶ መስቀል 38.7፣ካቺሲ 31፣ ማጀቴ 34.2፣ ማንኩሽ 33፣ ማሻ 60.4፣ አዳማ 31.4፣ 36.3፣ ፓዌ 37.5፣ ሰመራ 60.2፣ ተፒ41.2፣ 34.5፣ አዳሚቱሉ 31.2፣ አጋርፋ 32፣ 32.6፣ አሺ 30፣ ቢላምቢሎ 52.6፣ ደብረ ሲና 44.2፣ ደነባ 30.8፣ ጋሸና 32.3፣ 46.9፣ ጊሽራቤል 34.7፣ ጉንዶበረት 52.5፣ 30.5፣ 30፣ ሃሮ 40.2፣ 30.3፣ 30.5፣ 40.2፣ 30.5፣ 40.4፣ 50፣ ሂርና 30.2፣ ኮረም 34.5፣ ቁሉቢ 32.5፣ 37.4፣ መካነኢየሱስ 32.8፣ ሮቢት 31.4፣ እንዲሁም ሰቆጣ 38.4፣ 35.8፣ ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል። በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ53 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40.0-61.4 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ነቀምቴ፣ ማሻ፣ ሰመራ፣ ቻግኒ፣ ጊዳአያና፣ ቢላምቢሎ፣ ጉንዶ በረት፣ ጅማ፣ ሃሮ ይገኙበታል፡፡


Ethiopian Meteorology Institute

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከአፋር ክልል ፋንቲ፣ ሃዉሲ፣ ማሂ፣ ሃሪ እና ጋቢ ዞኖች ከጋምቤላ ክልል አኙዋክ፣ መዠንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ፣ አዲስ አበባ እና ደሬደዋ ላይ ከ41-285 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ሁሉም ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኙዋክ፣ መዠንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋና ባስኬቶ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ላይ በአብዛኛ መደበኛ እና በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ኦገሰት 1 እስከ 10/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ኦገሰት 1 እስከ 10/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ኦገሰት 1 እስከ 10/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች የተስፋፋ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን በማሻሻል እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ ሰብሎች እንዲሁም እንደ ስንዴ፣ ገብስ፣ አጃና ጤፍ ለመሳሰሉት የብርዕ ሰብሎች፣ የጥራጥሬና የቅባት እህሎች፣ የጓሮ አትክልቶች፣ ለቋሚ ተክሎችና በአረንጋዴ አሻራ መረሃ ግብር እየተተከሉ ለሚገኙ ዕጽዋቶች የውሃ ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነበረው። በተጨማሪም በተለያየ ምክንያት ዘግይተው የሚዘሩ የአጭር ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የመጠጥ ውሃ እና የግጦሽ ሳር አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በአንጻሩ ግን በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የአፈር መሸርሸርና በመሳዎች ላይ የውሃ መተኛት ለማስከተል የሚችል እንደነበረ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 4)።

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በተለይም በአባይ፣ በባሮ አኮቦ፣ ተከዜ፣ በላይኛውና በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ በገናሌ ዳዋ እና በዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ በጣም ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር ውሃ ሽፋን ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የወንዞችን ፍሰት እንዲጨምር፣ የግድቦችን የውሃ ክምችት እንዲያሻሽል እንዲሁም በተፋሰሶች ውስጥ የሚገኙ አነስተኛ የውሃ ማከማቻዎች በቂ የውሃ መጠን እንዲይዙ ከማድረጉም በተጨማሪ የከርሰ ምድር የውሃ መጠንም ሆነ የመስኖምና የሃይል ማመንጫ ግድቦች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የውሃ መጠን እንዲኖራቸው ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 5)።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## 2.1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በኦገስት የሁለተኛው አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ እየተስፋፉና እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛው፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው አህዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በተለይም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብእና መካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፉ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም፣ በሰሜን ምስራቅ፣ ምስራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ መካከለኛው፣ ምዕራብ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በሚቀጥሉት አስር ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከመካከለኛ እስከ ከባድ (ከ11-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በመካከለኛው፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 11-20/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 11-20, 2026 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን


ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፤ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ሸገር ሲቲ እና ሁሉም የሸዋ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ እና የምዕራብ ጉጂ ዞን | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም እናየአዊ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ዋግህምራ፣ የደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ | ከቀላል እስከ ከባድ መጠን (ከ1-30 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | አኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካካለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ በላይ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ ከባድ መጠን (ከ1-30 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅ፣ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች | ከቀላል እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| አፋር | የፋንቲ፣ አዉሲ፣ ማሂ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | አብዛኛው የክልሉ ዞኖች | ከቀላል መጠን እስከ ከባድ መጠን (ከ1-30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ እና ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ዞኖች | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |

## 2.2 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በኦገስት ሁለተኛው አስር ቀናት ከሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በኤሊ ዳር፣ ዱብቲ፣ ሰመራ፣ ቡሬ፣ አሳይታ፣ ሁንዱፎ፣ ገዋኔ፣ ሚሌ፣ ዳሊፋጊ፣ አይሻ፣ ጉሊና፣ አዋሽ አርባ፣ ባቲ፣ ዶሎ ኦዶ፣ ዳዋ፣ ጎዴ፣ አቦቦ፣ ቋራ፣ አዋሽ ፈንታሌ፣ ጭፍራ፣ ላሬ፣ መተሃራ እና ፉኙዶ አከባበዎች ላይ ከ26 እስከ 38 ዲግሪ ሴልሺየስ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8) ፡፡





ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 11-21, 2026, የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## 2.3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት ሁለተኛዉ አስር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀዳሚው አሥር ቀናት በበለጠ ሁኔታ እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ጊዜ ነው፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ለወንዞች ሙላትና ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

በመጪዎቹ የኦገስት ሁለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያዘም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ እና መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአህዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 9) ፡፡




ካርታ 9 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 21-31/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

Ethiopian Meteorology Institute

## 2.4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኦገስት የሁለተኛ አስር ቀናት በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገራችን አካባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው አፈር ውስጥ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል። በመሆኑም የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ ለመጠቀምና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የሚያስችል ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከወዲሁ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል (ሥንጠረዥ 2)፡ ፡

## 2.5 እ.አ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኦገስት አስር ቀናት የሚኖረው የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት በተለይም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሃገራችን ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ እጅግ በጣም ከፍተኛ መጠን የሚደረስ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል። በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት የሚኖሩ መልካም ዕድሎች በአግባቡ ለመጠቀምና አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ማለትም የጎርፍ መጥለቅለቅ፣ የመሬት መንሸራተት እንዲሁም የደራሽ ወንዝ ሙላትና ሌሎች ተያያዥ የተፈጥሮ አደጋዎች ለመቀነስ የሚከተሉትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል (ሥንጠረዥ 3) ፡፡

Ethiopian Meteorology Institute

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ እንዲሁም አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች | | | |
|---|---|---|---|
| **ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የተሰጠ ምክረ ሃሳብ** |
| ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፤ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ሸገር ሲቲ እና ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ የምዕራብ፣ መካከለኛው፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የአዊ ዞኖች፤ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፤ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ ዞኖች እና የአዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ዞኖች | ➢ የአፈር ዉስጥ እርጥበት መሻሻል<br>➢ ለረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገት እና ዘግተው የሚዘሩ ሰብሎችን ለመዝራት<br>➢ ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል<br>➢ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ለማጎልበት<br>➢ ለቋሚ ተክሎች እድገት እና ለከተማ ግብርና እንዲሁም<br>➢ ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜና ለአረንጓዴ አሻራ መረሃ ግብሮች | ➢ የእርጥበት መብዛት፣ የማሳዎች መጨቅየት እና ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውኃ በማሳዎች ላይ መተኛት<br>➢ ውሃገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ሰብሎች ላይ የአፈር መታጠብ<br>➢ ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎ ች የመሬት መንሸራተት<br>➢ የአረም መስፋፋት<br>➢ የሰብል በሽታና ተባይ መከሰት | ➢ የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም ዘግይተዉ የሚዘሩ የመኸር የአጭር ጊዜ ሰብሎችን መዝራት<br>➢ ተዳፋታማ ማሳዎች ላይ የተዘጉ የማፋሰሻና የማንጣፈፊያ ቦዮችን ማስተካከል<br>➢ የሰብል በሽታንና አረምን አስቀድሞ መከላከል፤<br>➢ የአፈር መሸርሸር መከላከል ስራዎችን በስፋት መስራት<br>➢ የመሬት መንሸራተት ተጋላጭነትን መቀነስ<br>➢ እርጥበት አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>➢ የማዳበሪያ አጠቃቀምን በትክክለኛው ሰዓት መተግበር<br>➢ አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር |

| ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| የምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ እና የምዕራብ ጉጂ ዞን፣ ዋግህምራ፣ የደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች እና የኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳድር ልዩ ዞን፤ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅ፣ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ የፋንቲ፣ አዉሲ፣ ማሂ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ አብዛኛዎቹ የሲዳማ ዞኖች፣ አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ➢ ሰብሎች ባልተዘሩባቸዉ አካባቢዎች የሚገኘዉን እርጥበት በመጠቀም የአጭር ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት<br>➢ የአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ፣ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል<br>➢ የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>➢ ለከተማ አካባቢ ግብርና ስራ | ➢ የዝናብ መቆራረጥና ደረቅ ሰሞናት መኖር<br>➢ የትነት መጠን መጨመር፤<br>➢ የሰብል በሽታ መከሰት፤<br>➢ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት ዝቅተኛ መሆንና<br>➢ ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን | ➢ የሚገኘዉን እርጥበት በቂ መሆኑን በማረጋገጥ ዘግይተዉ የሚዘሩ የአጭር ጊዜ የመኸር ሰብሎችን መዝራት<br>➢ የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>➢ የአፈር ውስጥ የትነት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤<br>➢ የአፈርና ውሃ እቀባ ስራን አስቀድሞ ማከናወን፤<br>➢ ለእንስሳት የግጦሽ ሣርን በአግባቡ መጠቀምና መጠበቅ፤ |

Ethiopian Meteorology Institute

ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| • አብዛኛው ተከዜ፣መረብ ጋሽ፣አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ በላኛዉ እና መካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ በላኛዉ የገናሌ ዳዋና በጥቂት የላይኛው ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች | • የገጸ-ምድር እና የከርሰ-ምድር ውሃ ሽፋን ይጨምራል። <br>• ለመስኖና ለኃይል ማመንጫ የሚውሉ ግድቦች የውሃ ክምችት መጨመር። <br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል። <br>• የውሃ ሀብት ተደራሽነትና የአካባቢ ኢኮኖሚ መሻሻል። | • ቅፅበታዊ ጎረፍ መከሰት <br>• የደለል ስጋት መጨመር <br>• የውሃ ብክለት መጨመር <br>• የውሃ ማፋሰሻ ቱቦዎች በቆሻሻ መዘጋት | • የዝናብ ውሃ ማሰባሰብና ማጠራቀም <br>• የመጠጥ ውሃን አክሞ መጠቀም <br>• የፍሳሽ መውረጃ ቦዮችን ማፅዳት <br>• የጎርፍ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት ወቅታዊ የአየር ትንበያዎችንና ምክረ ሀሳቦችን በየጊዜው መከታተል |
| **ከቀላል እስከ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| • የታችኛው አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ አይሻ፣ የላይኛው ዋቢ ሸበሌና የባሮ አኮቦ ተፋሰሶች | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል <br>• የጎርፍም ሆነ የደለል ስጋት መቀነስ <br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • ከፍተኛ ትነት <br>• ዝቅተኛ የውሃ ፍሰት <br>• እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች መጠነኛ የውሃ እጥረት | • የሚገኘውን የዝናብ ውሃ አክሞ መጠቀም <br>• የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም <br>• ከቤት ጣራ ላይ ውሃ የመሰባባሰብና ማጠራቀም ስራዎች <br>• የአየር ሁኔታ መረጃን በቅርበት መከታተል |
| **ደረቅ የአየር ሁኔታ** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| ኦጋዴን፣ የመካከለኛውና ታችኛው ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች | • <br>• የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል <br>• | • የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት መቀነስ <br>• የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎች የውሃ መጠን መቀነስ <br>• የከርሰ ምድር የውሃ ሃብት መቀነስ <br>• የትነት መጠን መጨመር | • የውሃ እጥረት በሚገጥማችው አካባቦዎች የውሃ ተደራሽነትን ማረጋገጥ <br>• የሚገኘውን ውሃ በቁጠባና በአግባቡ መጠቀም <br>• የገጸ ምድር የውሃ ሀብትን በአግባቡ መያዝ |